በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር

# የክረምት ወቅት አጋማሽ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና ያሳደረዉ ተፅዕኖ

## እንዲሁም ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምበር 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

ምዕራፍ አንድ ... - 5 -

1.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ... - 5 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ... - 8 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ... - 8 -

ካርታ3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ... - 9 -

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ... - 9 -

ምዕራፍ ሁለት ... - 9 -

2..1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምበር 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ... - 9 -

ካርታ 4ሀ እ.ኤ.አ በኦገስት 2024 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ ... - 11 -

ካርታ 4ለ እ.ኤ.አ በሴፕቴምበር 2024_የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ ... - 11 -

ምዕራፍ ሦስት ... - 11 -

3.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... - 11 -

ካርታ 5 ሀ እ.ኤ.አ ጁን 2024 የእርጥበት_ደረጃ ጠቋሚ ... - 13 -

ካርታ 5 ለ እ.ኤ.አ ጁላይ 2024 የእርጥበት_ደረጃ ጠቋሚ ... - 13 -

3.2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... - 13 -

ካርታ 6ሀ በጁን ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን ... 14

ካርታ 6ለ በጁላይ ወር በተፋሰሶች_ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን ... 14

3.3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... - 14 -

ካርታ 7ሀ በጁን ወር ለወባ መፈጠር_ምቹ የሆነ የአየር ጠባይ ... - 15 -

ካርታ 7ለ በጁላይ ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የሆነ የአየር ጠባይ ... - 15 -

ካርታ 8ሀ. በጁን ወር አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ ... - 16 -

ካርታ 8ለ. በጁላይ ወር አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ ... - 16 -

ምዕራፍ አራት ... - 16 -

4.1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምበር 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... - 16 -

4.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምበር 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... - 17 -

4.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምበር 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... - 18 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የክረምት ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

## አጠቃላይ

የክረምት ወቅት ከጁን እስከ ሴፕቴምበር ያሉትን ወራት የሚያካትት ሲሆን፤ በወቅቱ ከሚኖረው የዝናብ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው በጁላይና በኦገስት የሚጥለው ዝናብ ነው። በዚህ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው የዝናብ መጠን የሚኖረው በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፤ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ አካባቢዎች ላይ ነው።

በመደበኛ ሁኔታ በሀገሪቱ የክረምት ዝናብ ከጁን ወር ጀምሮ መዝነብ የሚጀምር ሲሆን፤ በአወጣጥ ረገድ ደግሞ ከሰሜን ምዕራብ በሴፕቴምበር መጨረሻ እንዲሁም ከምዕራብና ከደቡብ ምዕራብ ከኖቬምበር አጋማሽ በኋላ ነው። የዝናቡ ሥርጭት ከወቅቱ መግቢያ ጀምሮ ቀስ በቀስ ከምዕራብ ወደ ሰሜን፤ መካከለኛ፣ ምሥራቅና ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ እየተስፋፋ የሚሄድ ሲሆን፤ በመካከለኛው ኢትዮጵያ ላይ በጁን ሁለተኛው ሳምንት እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በጁን የመጨረሻ ሳምንት ወይም በጁላይ የመጀመሪያው ሳምንት ይጀምራል። የወቅቱ ዝናብ ሲወጣም ከዓመት ዓመት ከቦታ ቦታ ይለያያል። በዚህ ረገድም የወቅቱ ዝናብ ከሰሜን ምስራቅ በሴፕቴምበር የመጀመሪያው ሳምንት ላይ የሚወጣ ሲሆን፤ በመካከለኛውና በምስራቅ ኢትዮጵያ ላይ እስከ ሴፕቴምበር መጨረሻው ሳምንት ድረስ ይቆያል።

በተተነተኑና በተተነበዩ የውቅያኖስና የከባቢ አየር ክስተቶች ላይ ትንታኔ በማካሄድ የጥናቶቹ ውጤትም ለክረምት ወቅት ለተሰጠው የአየር ጠባይ ትንበያ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በዚህም መሰረት የተካሄደዉ ትንታኔዎችንና የተለያዩ የአየር ጠባይ የትንበያ ሞዴል ውጤቶችን መሰረት በማድረግ፤ በመጪው ክረምት ወቅት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ሊኖር የሚችለው የዝናብ መጠንና ሥርጭት ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎችን በሰፊው በመዳሰስ የወቅቱ ትንበያ ተጠቁሞ ነበር፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

በዚህ ፁሁፍ ያለፈዉ የክረምት ሁለት ወራት (ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31) የአየር ጠባይ ግምገማና የቀጣዩ ሁለት ወራት (ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምበር 30) አዝማሚያን ግንዛቤ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

የዘንድሮው ክረምት የአየር ጠባይ ትንበያ በተሰጠበት ወቅት በአሁኑ ጊዜ የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ ምስራቃዊውና የመካከለኛው ክፍል ከመደበኛው በታች የባህር ወለል ሙቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በቀጣዮቹ የክረምት ወራትም ከመደበኛው በታች የመቀዝቀዝ ሁኔታው ቀጣይነት መኖር ዕድል እስከ 69% ሊደርስ እንደሚችል ግንዛቤ መወሰዱ ይታወሳል። በተጨማሪም ከደቡባዊው የህንድ እና የአትላንቲክ ውቅያኖሶች የላይኛዉ የዉሃ ወለል ሙቀት መሞቅ በክረምት ዝናብ መጠንና ስርጭት ላይ በአብዛኛው አዎንታዊና አሉታዊ ሁኔታ እንደሚፈጥር ግንዛቤ ተወስዶ ነበር። ከዚሁ ጋር ተያይዞም የዘንድሮ የክረምት ዝናብ በመጠንም ሆነ በቦታ ሽፋን በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመደበኛው በላይና መደበኛ ሊሆን እንደሚችልና አልፎ አልፎም ቅጽበታዊ ጎርፍና የወንዞች ሙላት ሊያጋጥም እንደሚችል ተጠቁሞ ነበር። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሀገሪቱ ሰሜን፣ ሰሜን ምዕራብና ሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የክረምቱ ዝናብ የመጠናከር አዝማሚያ እንደሚያሳይ ቅድመ ትንበያ ተሰጥቷል። እስካሁን ከተሰበሰቡት የዝናብ መረጃዎች ለመገንዘብ እንደተቻለው የዘንሮው የክረምት ዝናብ በአጀማመር ረገድ መደበኛውን ፈር የተከተለ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚዎችን እያዳረሰ ከመሆኑም ሌላ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ወራት ሊኖር የሚችለው የአየር ጠባይ አዝማሚያ እንዲሁም በግብርናው በዉሃ ሴክተሮች እና በጤና ላይ አሳድሮ የነበረውን ዳሰሳ እንዲሁም ወደፊትም ሊፈጥር በሚችለው ተፅዕኖ ላይ ጽሁፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ተፅዕኖ ያላቸው የባህርና የከባቢ አየር ገፅታዎች ቀደም ሲል በተሰጠው ትንበያ መሠረት በተመሳሳይ መልኩ ተስተውለዋል፡፡ የክረምት ዝናብ ሰጪ ክስተቶችም በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ምቹ ሁኔታን በመፍጠራቸው የዘንድሮው ክረምት አጀማመሩ በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ቀደም ብሎ የጀመረ ሲሆንና በአንብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ ደግሞ መደበኛ ፈሩን ተክትሎ ጀምሯል፡፡ በተጨማሪም በሶስተኛው የጁን አሥር ቀናት ከዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መጠናከር ጋር በተያያዘ የዝናቡ ስርጭት ወደ አብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ተስፋፍቶ ተስተውሏል።

ከጁን ሁለተኛው አስር ቀናት ጀምሮ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎቹ ላይ ተወስኖ የነበረው ዝናብ ወደ አብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎቹ ተስፈፍቶ ታይቷል። በመሆኑም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በምስራቅ፣ በመካከለኛው እና በምዕራብ ኦሮሚያ፤ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል፤ በመካከለኛው እና ምዕራብ አማራ፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በሲዳማ ክልል ዞኖች እና አዲስ አበባ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በጁን ሶስተኛው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ይበልጥ ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ የዝናብ ሁኔታ ነበራቸው፡፡

በአጠቃላይ በጁን ወር የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ አግኝተዋል፡፡በተለይም በጁን ወር 51 በሚደርሱ ጣቢያዎች ላይ ከ30-118 ሚ.ሜ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በአዲስ አበባ ቦሌ 46.5፤ በአርባ ምንጭ 43.0፤ በአቦምሳ 36.5፤ በአለም ተፈሪ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

41.4፤ በአርጆ 36.2፤ በአልጌ 55.0፤ በአይከል 30.0፣ 37.9 እና 37.8፤ በአይራ 46.2 እና 53.4፤ በአሶሳ 49.5፣ 54.0 እና 51.7፤ በአፅቢ 40.0፤ በባህርዳር 34.2 እና 32.5፤ በቻግኒ 35.0፤ በጭራ 41.0 እና 83.0፤ በዳንግላ 33.7፤ በደባርቅ 87.2 እና 50.0፤ በደብረ ማርቆስ 36.6፤ በእምድብር 31.4፤ በኢጃጂ 31.2፤ በፍቼ 32.6 እና 38.1፤ በጎሬ 34.0 እና 45.3፤ በጎንደር 31.5፤ በነቀምቴ 34.5፣ 76.1፣ 31.1 እና 44.3፤ በአማን 30.5 እና 32.2፤ በአንገር ጉትን 35.0፣ 32.0 እና 35.2፤ በቡሬ 40.6፤ በጭራ 35.4፤ በጊምቢ 68.74፣ 46.3 እና 31.9፤ በጊዳ አያና 61.4፤ በካቺሴ 50.5፣ 32.6 እና 33.0፤ በላይበር 56.5 እና 31.0፤ በሊሙ ገነት 44.7፣ 72.0 እና 87.7፤ በመካነ ሰላም 32.1፤ በማሻ 40.2 እና 40.6፤ በመተሃራ 52.3፤ በማጀቴ 31.8፤ በመተማ 32.2 እና 32.7፤ በነጆ 30.5፤ በአዳማ 32.8፤ በተርጫ 35.8፤ በሰኮሩ 30.0፤ በሻምቡ 37.7 እና 32.1፤ በሽሬ 35.4 እና 30.5፤ በባቱ 40.5 እና 31.6፤ በወራቤ 47.2፤ በወረኢሉ 33.7፤ በየትኖራ 30.4፤ በጉብሬ 49.5፤ በግራዋ 35.0፤ በሂርና 32.6፤ በኮምቦልቻ (ምስራቅ ሀረርጌ) 38.8 እንዲሁም በጨለንቆ 30.4 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

በጁላይ ወርም ለክረምት ዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ይበልጥ የተጠናከሩበትና የተስፋፉበት ወር ነበረ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመጀመሪያው እና በሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት የነበራቸው ቢሆንም፤ በአንጻሩ ግን በሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ይበልጥ ተጠናክረው ተስተውለዋል፡፡ ስለሆነም በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ በጁላይ ወር የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ተደጋጋሚነት ያለው ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተለይም አንድ መቶ አስራ ስምንት (118) በሚደርሱ የሀገራችን አከባዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 44.0፣



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

በባህርዳር 67.8፣ በቢሾፍቱ 42.5 እና 41.5፣ በጎሬ 47.7፣ በጅማ 59.6፣ በአዲግራት 43.7፣ በአለም ከተማ 43.0፣ በአምባ ማሪያም 42.4፣ በአርሲ ሮቤ 74.2፣ በአይራ 46.8፣ 58.6 እና 53.2፣ በአማን 47.4 እና 58.8፣ በአምደወርቅ 42.5፣ በአንገር ጉትን 48.4፣ በአዴት 69.4፣ በአዋሽ አርባ 60.0 እና 50.0፣ በቡለን 60.4፣ በቡሌ ሆራ 40.0፣ በቻግኒ 42.1፣ በጨፋ 44.2፣ በጭራ 55.5 እና 64.9፣ በዳንግላ 72.0፣ 43.3 እና 47.2፣ በደባርቅ 44.0፣ በደብረ ብረሃን 43.6 እና 47.8፣ በፉኚዶ 42.5፣ በጋምቤላ 46.2፣ በጊዳ አያና 46.1 እና 67.3፣ በሀረር 40.0 እና 53.0፤ በካቺሴ 56.6፤ በላይበር 54.7፣ በማጀቴ 40.9፣ በሜኢሶ 40.2፣ በሞጣ 50.8፣ በአዳማ 41.0 እና 63.8፣ በፅፅቃ 46.2፣ በወላይታ 44.1፣ በፓዌ 51.3 እና 51.6፣ በሰኮሩ 41.8፣ በስንቃጣ 42.0፣ በሻውራ 43.8፣ በሾላገበያ 40.7፣ በቴፒ 62.3፣ በያበሎ 68፣ በየትኖራ 41.7፣ በባቱ 44.4፣ በላንጌ 68.5 እና 56.0፤ በቁለቢ 42.6 እና 46.6፣ በካራሚሌ 50.2፣ በጨለንቆ 47.9፣ በግራዋ 49.5 እንዲሁም በጉብሬ 45.7 እና 43.2 በሚ.ሜ ይገኙበታል። በተጨማሪም ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከ70 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ጣቢዎች በአፅቢ 112.0፣ በዳሊፋጊ 117.3፣ በእነዋሪ 118.0፣ በቡለን 100.2፣ በጨለንቆ 90.4፣ በባቱ 74.0፣ በላሬ 78.0፣ በጋምቤላ 76.6፣ በወሊሶ 72.0 እንዲሁም በጊዳ አያና 78.3 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት ሁለት ወራት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ዋህግምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ እንዲሁም ባሌ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ መተከል፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን እና ሲቲ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ ዞኖች፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ሀላባ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ኮንታ፣ ከፋ፣ ሸካ እና ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር

ጌዲኦ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ከንሶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ ከ40-650 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በዝናብ ቀናት ስርጭት ረገድም ከ 10-57 ቀናት ያህል የክረምት ዝናብን አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2)፡፡


በአጠቃላይ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የዘነበው ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ሲገመገም ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ዋህግምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ እንዲሁም ባሌ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ መተከል፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል ፋፉን እና ሲቲ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ ዞኖች፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ሀላባ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ኮንታ፣ ከፋ፣ ሸካ እና ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ከንሶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት




ካርታ3 ኢ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. 1 ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ ሴፐቴምበር 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በይበልጥ የሚጠናከሩበት ወር ሲሆን፤ ዝናቡም በመጠንም ሆነ በስርጭትረገድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን በስፋት ያዳርሳል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ተጠናክረው ከሚፈጠሩት ዝናብ ሰጭ ቁልል ደመናዎች ነጎድጓዳማና በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ አልፎ አልፎ በመደበኛ ሁኔታ ይከሰታል። በሌላ በኩል በሴፐቴምበር ወር ከክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራብና ደቡብ ኢትዮጵያ ቀስ በቀስ ማፈግፈግ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የክረምቱ ዝናብ ቀስ በቀስ ከምስራቃዊው አጋማሽና ከመካከለኛው ኢትዮጵያ እየቀነሰ በመሄድ በምዕራባዊው አጋማሽ ግን ከሞላ ጎደል መዝነብ የሚቀጥል ሲሆን፤ በተጨማሪም ወቅታዊው እርጥበት አዘል አየር ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚስፋፋበት ወር ነው።

በመጪዎቹ ኦገስት እና ሴፐቴምበር ወራት አሁን በመታየት ላይ ያለው የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ ምስራቃዊና መካከለኛው የባህር ወለል ሙቀት ከመደበኛ በታች (ENSO-LA NINA) የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ እንደሆነ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

ቀደም ብሎ የክረምት ትንበያው በተሰጠበት ጊዜ በሰሜን አትላንቲክ፤ በህንድ የደቡብ ምስራቅ ውቅያኖሶችና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የውሀ አካሎች ላይ ይታይ የነበረው የባህር ወለል ሙቀት መሞቅ ( positive IOD) ወደ ከመደበኛ በታች (Negative IOD) በሚቀጥሉት ወራትም ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ተወስዷል።


በመሆኑም በሚቀጥሉት የኦገስትና የሴፕቴምበር ወራት ከአትላንቲክና ከህንድ ውቅያኖስ የሚገባው እርጥበት አዘል የአየር ሁኔታ በተለይም በሰሜንና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ሆኖ ሊቀጥል እንደሚችል ከመጠበቁም በላይ በኦገስት ወር በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በፀሐይ ሀይል ተጠናክረው ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ አልፎ አልፎ ይኖራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በሴፕቴምበር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች የፀሀይን አቅጣጫ ተከትለው ወደ ደቡብ ማፈግፈግ ስለሚጀምሩ በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የበጋው ዝናብ ቀስ በቀስ መጣል ይጀምራል፡፡

በዚሁ መሰረት በመጪዎቹ ሁለት የክረምት ወራት ምዕራብ ትግራይና አማራ፤ ቤንሻንጉል ጉምዝ፤ ጋምቤላ፤ ምዕራብ ኦሮሚያና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ የመካከለኛውና የደቡብ ትግራይ፤ የምስራቅ አማራ፤ የመካከለኛው ኦሮሚያ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ፤ አፋር፤ አዲስ አበባ እንዲሁም ድሬዳዋና ሐረሪ ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም ምስራቅ ኦሮሚያ፤ ሰሜን ሶማሌና የሲዳማ ክልል ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ ያገኛሉ። በሌላ በኩል ከሴፕቴምበር አጋማሽ በኋላ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ ቆላማ አካባቢዎች ወቅታዊው የበጋ ዝናብ እንደሚጀምር የሚጠበቅ በመሆኑ፤ የተጠቀሱት ሥፍራዎች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ የማግኘት ከፍተኛ ዕድል ይኖራቸዋል። በአወጣጥ ረገድም የክረምቱ ዝናብ ከመደበኛው ጊዜ ዘግይቶ እንደሚወጣ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ(ካርታ 4 ሀ እና ለ)፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

በነሃሴ ወር




ካርታ 4ሀ እ.ኤ.አ በኦገስት 2024 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በመስከረም ወር




ካርታ 4ለ እ.ኤ.አ በሴፕቴምበር 2024 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

# ምዕራፍ ሦስት

## 3.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት የተገኘው የእርጥበት መጠን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ለመኸር የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረዉ፡፡ በጁን ወር የተገኘው የዝናብ መጠን የአፈርን እርጥበት ከማሻሻልም አልፎ ከሰኔ ጀምሮ የዘር ጊዜና የማሳ ዝግጅት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በወቅቱ ለመዝራት አመቺ ሁኔታ የነበረው ሲሆን፤ አስቀድመው ተዘርተው ፍሬ በማፍራት ላይ ለነበሩ የበልግ ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ሚና ከመኖሩም በላይ ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደበቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምስራቅ እና በምስራቅ የአርብቶ አደርና ከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው እርጥበት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት አንፃር አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ እንዲሁም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et


በነበሩ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰት የነበረ ቢሆንም፤ በግብርናዉ አንቅስቃሴ ላይ ያደረሰዉ አሉታዊ ተፅዕኖ አልነበረም።

በጁላይ ወር የተገኘዉ እርጥበት በአብዛኛዉ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ አካባቢዎችን ያዳረሰ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻልም አልፎ ከጁላይ ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ለመዝራትና አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ሚና ከመኖሩም በላይ ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ ቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር በጎ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከፍተኛና ተከታታይነት የነበረው እርጥበት ለጎርፍ መከሰትና በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ያስከተለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በጎፋ፣ በደሴ፣ በሲቲ፣ በማዕከላዊ ሲዳማ እንዲሁም በጅማ እና በምዕራብ አርሲ ዞን ከነበረው ከባድ ዝናብ እና ተከታታይ የዝናብ ቀናት ጋር ተያይዞ የመሬት መንሸራተትና ጎርፍ የተከሰተ ሲሆን፤ በንብረት፣ በሰው ህይወት፣ በሰብሎችና በእንስሳት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡


በአጠቃላይ ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት (ጁን እና ጁላይ) የእርጥበት ሁኔታ በእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ሁኔታ አብዛኛው ለመኸር አብቃይና ተጠቃሚ አከባቢዎች አዎንታዊ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ፣ በቡቃያ እና በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፤ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ እና በምስራቅ አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 5ሀ እናለ)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et



ካርታ 5 ሀ እ.ኤ.አ ጁን 2024 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ





ካርታ 5 ለ እ.ኤ.አ ጁላይ 2024 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ

## 3.2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍናቸው ሁለት የክረምት ወራት በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የውኃ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው። ከዚህም ጋር ተያይዞ በጁን ወር የተገኘው የእርጥበት መጠን በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የሳደረውን ተጽዕኖ ስንመለከት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአብዛኛው በአባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣ የላይኛው እና መካከለኛው አዋሽ እንዲሁም የላይኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በጁላይ ወር የእርጥበቱ ሁኔታ በመጠንም ሆነ በስርጭት በመስፋፋት በአብዛኛው በአባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ተከዜ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ አፋር ደናክል፣ በላይኛው እና በመካከለኛው ገናሌ ዳዋ እንዲሁም በላይኛው ዋቤ ሸበሌ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት መጠን እንዲኖራቸው ያስቻለ እንደነበር የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮልጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተጨማሪም በጥቂት የመካከለኛው አዋሽ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ስምጥ ሸለቆ

እንዲሁም በታችኛው ኦሞ ጊቤና ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የነበረው የተሻለ የእርጥበት፣ የገጸምድርንና የከርሰ ምድርን የውሃ ሀብት ከማበልጸግ አንጻር አዎንተዊ አስተዋፅዖ የነበረው ሲሆን፤ ከባለፈው የጁን ወር አንጻር በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ ነበር፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱ የክረምት አጋማሽ ወራት በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ ይህም ወደ ግድቦች እና ወንዞች የሚገባውን የውሃ መጠን በማሳደግ ለሀይል ማመንጫ እና ለመስኖ ስራ በቂ የውሃ ሀብት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር በጎ ጎን ነበረው። በአንጻሩ ግን ተከከታታይነት ከነበረው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በብዙ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የቅጽበታዊ ጎርፍ እና የወንዞች ከገደብ በላይ መሙላት ጋር ተያይዞ በሰው ህይወት፣ በንበረት እና በመሰረተ ልማት ላይ ጉዳት አድርሷል (ካርታ 6ሀ እና ለ)።



ካርታ 6ሀ እ.ኤ.አ በጁን ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን




ካርታ 6ለ እ.ኤ.አ በጁላይ ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን

## 3.3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በጁን ወር የነበረው የአየር ጠባይ ለወባ ተጋላጭ በሆኑ የምዕራብ ኦሮሚያ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የምዕራብ አማራ፣ ምስራቃዊ ጋምቤላ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና ጥቂት የትግራይ ክልል ቦታዎች ላይ ለወባ መፈጠር ምቹ የሆነ የአየር




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et


ጠባይ እንደነበራቸው የተተነተኑት የጤና ሚቲዎሮሎጅ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7ሀ) ።

በጁላይ ወር ላይ የነበረው የአየር ጠባይ ለወባ ትንኝ መራባት የነበረው ምቹነት የወባ ተጋላጭ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባለፈው የጁን ወር በበለጠ ሁኔታ ተስፋፍቶ የነበረ ሲሆን፣ በተለይም በአብዛኛው የኦሮሚያ ክልል፣ የደቡብና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ የሲዳማ ክልል፣ የጋምቤላ ክልል፤ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ አብዛኛው ምዕራብ አማራና የምስራቅ አማራ አካባቢዎች፣ የትግራይ ክልል፣ አብዛኛው የአፋር ክልል፣ መካከለኛው የሶማሌና አጎራባች ቦታዎች እንዲሁም የድሬዳዋና ሀረሪ ክልል ለወባ ትንኝ መራባት ምቹ የአየር ጠባይ ነበራቸው (ካርታ 7ለ)። በአጠቃላይ ባሳለፍናቸው ሁለት የክረምት አጋማሽ ወራት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የወባ በሽታ ክስተት እንደነበረ ከተለያዩ አካባቢዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም በጁን እና በጁላይ የታየው የወባ በሽታ መስፋፋት በአብዛኛው ከባለፈው የኤፕሪል ወር ጀምሮ ለወባ መራባት ምቹ የነበረው የአየር ጠባይ እንደ አንድ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል።

በሌላ በኩል በክረምት የመጀመሪያ አጋማሽ ወራት የነበረውን የሙቀት ሁኔታ (Heat Stress) በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለሰዎች ተስማሚ የሆነ የአየር ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ነገር ግን በአፋር፣ በጋምቤላ እና በጥቂት የሶማሌ ደቡባዊ ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ጥንካሬ የነበረው የሙቀት ሁኔታ (Heat Stress) እንደነበረ የተሰበሰቡና የተተነተኑ የጤና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8 ሀ እና ለ) ።





ካርታ 7ሀ በጁን ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የሆነ የአየር ጠባይ




ካርታ 7ለ በጁላይ ወር ለወባ መፈጠር ምቹ የሆነ የአየር ጠባይ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 8ሀ. በጁን ወር አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ



ካርታ 8ለ. በጁላይ ወር አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ

# ምዕራፍ አራት

## 4.1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምበር 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ለመጪዎቹ ሁለት ወራት (ኦገስት እና ሴፕቴምበር) በቂ የእርጥበት መጠን የመኸር አብቃይና ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ለእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አመቺ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በመኸር ወቅት ለሚመረቱ ለመካከለኛና ረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ ዘግይተዉ ለተዘሩ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ለሚገኙ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት አውንታዊ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ሆኖም ከመደበኛ በላይ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ አካባቢዎች በመጪው ኦገስት ካለፈው ጁላይ ወር በተሻለ ሁኔታ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፋፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚሰጥ ምክረ ሀሳብ መሰረት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች በሚኖረው ከባድ ዝናብ እና ተከታታይ የሆነ የዝናብ ቀናት ጋር ተያይዞ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተትና በጎርፍ የመጠቃት ሊከሰት ስለሚችል ለዚህ ተጋላጭ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

የሆኑ አካባቢዎች ተገቢዉን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡ በአጠቃላይ በተቀሩት የክረምት ሁለት ወራት(ኦገስት እና ሴፕቴምበር) እርጥበቱ በመጠንም ሆነ በስርጭት በአብዛኛው የክረምት አብቃይና ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከእርጥብ እስከ በጣም እርጥብ ሆኖ እንደሚቆይ ይጠበቃል፡፡

## 4.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምበር 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ሁለት የክረምት ወራት (ኦገሰት እና ሴፕቴምበር) በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው እየተሰፋፋና እየጨመረ እንደሚሄድ በትንበያው ተገልጿል፡፡ በዚህም መሰረት የክረምት የእርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ አዋሽ፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተስፋፋና የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር የውሃ ሀብትን ከማጎልበት አኳያ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያየዞ ወደ ግድቦች እና የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከፍ እንደሚያደርገው የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ ሰፊ የውሃ ሀብት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር የጎላ ሚና ይኖረዋል።

ሆኖም ግን ከባለፉት የበልግ ወራት ጀምሮ በጁን እና በጁላይ ወደ ተለያዩ ግድቦች እየገባ ከነበረው እና በሚቀጥሉት ሁለት ወራት ከሚጠበቀው የዝናብ መጠን ጋር ተዳምሮ የውሃ ከፍታ መጠናቸውን ሊያሳድገው ስለሚችል በግድቦች ዙሪያ የቅርብ ክትትል እንዲደረግ እንመክራለን። በሌላ በኩል ከሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት እና ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ ከላይ በተጠቀሱት ተፋሰሶች እና ንዑስ ተፋሰሶች ላይ የቅጽበታዊ ጎርፍና የወንዞች ሙላት በከተሞች፣ ተዳፋታማና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ሊከሰት ስለሚችል ህብረተሰቡና የሚመለከታቸው አካላት በሰው ህይወትም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አስፈለጊውን ቅድመ ጥንቃቄ እንዲደርጉ እንመክራለን፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

### 4.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ ሴፕቴምበር 30/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ ሁለት የክረምት አጋማሽ ወራት የሚጠበቀው የአየር ጠባይ በጤናው ላይ የሚኖረው የተጽዕኖ ስንመለከት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገራችን ክልሎች ላይ ለወባ ትንኝ መፈጠርና መስፋፋት አመቺ የአየር ሁኔታ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ አብዛኛው የአማራ ክልል፤ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፤ አብዛኛው የኦሮሚያ ክልል፤ የጋምቤላ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ ሲዳማ ክልል፣ ሰሜናዊ የሶማሌ ክልል፣ አብዛኛው የደቡባዊ የአፋር ክልል፣ እንዲሁም የሀረሪ ክልል እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በአብዛኛው ቦታዎቻቸው ላይ ለወባ ትንኝ መራባት ምቹ የሆነ የአየር ጠባይ ይኖራቸዋል። በመሆኑም ለወባ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎችም ሆኑ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ይህንን የጤና ሚቲዎሮሎጂ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መልዕክት መሰረት በማድረግ የወባ ተጋላጭነትን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስ የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ከወዲሁ ማከናወን ተገቢ ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ ለወባ ትንኝ መራቢያነት የሚያመቹ ሁኔታዎችን የማስወገድ፣ የማጽዳት እና የወባ ትንኝ መከላለከያ አጎበሮችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ይመከራል። በተጨማሪም በክረምት የመጀመሪያዎቹ አጋማሽ ወራት የነበረውና በመጪዎቹ ሁለት ወራት ለወባ ትንኝ መራባት የሚኖረው ምቹ የአየር ሁኔታ በቀጣዩ የበጋ ወራት ለወባና ለደንጉ ፊቨር ስርጭት ምቹ ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል ከወዲሁ ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድግ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከሚጠበቀው ከፍተኛ የዝናብ መጠን ጋር ተያይዞ እንደ ኮሌራ ላሉ የውሃ ወለድ በሽታ መስፋፋት ምቹ ሁኔታን ሊፈጠር ስለሚችል ማህበረሰቡም ሆነ የሚመለከታቸው ባለድረሻ አካላት ለውኃ ወለድ በሽታ ያለውን ተጋላጭነት ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማከናን ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et